# ዜና መጽሄት




የካቲት 2016 ዓ.ም

## በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለስልጣን

**በህዝብ ግንኙነትና ኮሙዩኒኬሽን**

**የተዘጋጀ**


## አድራሻ

**ፌስቡክ** : https://www.facebook.com/oficialpageofECA/

**ቴሌግራም**:- https://t.me/Ethiopiaconstructionaouthority

**ዌብሳይት**:- www.eca.gov.et

**ፖ.ሳ.ቁ**:- 12201

## የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለስልጣን

### ራዕይ

“በ2022 በተጠናከረ የቁጥጥር ስርዓት የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው በአፍሪካ ተወዳዳሪ ሆኖ ማየት!”

### ተልዕኮ

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ የግንባታ ፕሮጀክቶች በተገቢው ወጪ፣ ጊዜ ጥራት መፈጸሙን እንዲሁም የዜጎችን ፣ የአካባቢ ደህንነትንና ጤንነትን መጠበቁን በማረጋገጥ ዜጎችን ተጠቃሚ ማድረግ ነው፡፡



### አድራሻ

**ፌስቡክ** : https://www.facebook.com/oficialpageofECA/

**ቴሌግራም**:- https://t.me/Ethiopiaconstructionaouthority

**ዌብሳይት**:- www.eca.gov.et

**ፖ.ሳ.ቁ** 12201

## የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለስልጣን በ2016 ግማሽ በጀት ዓመት ተቋሙ ከተቋቋመበት ዓላማ አንጻር ያከናውናቸው ቁልፍ ተግባራት

### በስድስት ወር ውስጥ እየተከናወኑ የሚገኙ ተግባራት

- የኮንስትራክሽን ምዝገባና ብቃት ማረጋገጫ ስራዎች ሙሉ በሙሉ በኤሌክትሮኒክስ አገልግሎት E- Service መስጠት ተጀምሯል፡፡ የኩባንያ ባለቤቶች ለአድሳት ሲያመለክቱ ፕሮጀክቶቻቸውን በE- Service እንዲያስመዘግቡ አስገዳጅ ከመደረጉም ባለፈ የፕሮጀክት ምዝገባ ሒደቱን ከክፍያ ስርዓቱ ጋር ለማስተሳሰር ከገንዘብ ሚኒስቴር ጋር እየተሰራ ይገኛል፡፡
- የክልሎች የኮንስትራክሽን ምዝገባ ሒደት ላይ ድጋፍ በጅግጅጋ፣ አፋርና ሲዳማ ክልሎች ድጋፍ በማድረግ ለሌሎች ክልሎች ተሞክሮ በሚሆን ደረጃ ረቂቅ ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡
- የባለሙያ ምዝገባ በግማሽ ዓመቱ 12368 ተገልጋዮች አመልክተው ለ8999 ባለሙያዎች አገልግሎቱን ሲያገኙ 3369 ሂደት ላይ ናቸው፡፡
- የኩባንያ ምዝገባ 3911 ተገልጋዮች አመልክተው 3813 ኩባንያዎች አገልግሎቱን አግኝተዋል፡፡
- በግንባታ ፕሮጀክት ዲዛይን ቁጥጥር ስራ 51 የህል የግንባታ ፕሮጀክት ዲዛይኖች (የህንፃ ዲዛይኖች፣ የስፖርት ማዘውተሪያ ስቴድየም፣ የምድረ-ገፅ ማስዋብ፣ የውሃ ትሪትመንት ፕላንት እና የውስጥ ለውስጥ መንገድ የዲዛይን ሥራዎች) ተገምግመው በኢትዮጵያ ኮድ እና ስታንዳርድ መሠረት የማስተካከያ እርማት ለሚያስፈልጋቸው ግብረ-መልስ ተሰጥቷቸዋል፤
- ፕሮጀክቶች ላይ የዋጋ ተገማችነት/ Cost Predictability 51 የተቀመሩ የፕሮጀክት ዋጋዎችን በመገምገም እርማትና ማስተካከያ የሚያስፈልጋቸውን እንዲስተካከሉ ተደርጓል፡፡
- በውሃና ኢነርጂ ፕሮጀክት ዲዛይን ግምገማ ስድስት 6 የሚሆኑ በፌደራል መንግስት ባለቤትነት የሚገነቡ የመስኖ ግንባታ ፕሮጀክት ዲዛይኖች ተገምግመው አስገዳጅ በሆነው የኢትዮጵያ ኮድ እና ስታንዳርድ መሠረት የማስተካከያ እርማት ለሚያስፈልጋቸው ግብረ-መልስ ተሰጥቷቸዋል፡፡
- የትራንስፖርትና ኮሙዩኒኬሽን ግንባታ ፕሮጀክቶች ዲዛይን ግምገማ ሶስት የሚሆኑ በፌደራል መንግስት ባለቤትነት የሚገነቡ ፕሮጀክቶች ዲዛይን ተገምግመዋል በሒደቱም አስገዳጅ በሆነው የኢትዮጵያ ኮድ እና ስታንዳርድ መሠረት የማስተካከያ እርማት ለሚያስፈልጋቸው ግብረመልስ ተሰጥቷቸዋል፡፡

# መጪው ዘመን ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ብርሃናማ ነው።

ዓለማችን ከጊዜ ወደ ጊዜ የጤና፣ የጂኦ ፖለቲካል እና የምጣኔ ሃብት ቀውሶች ሲፈራረቁባት ይስተዋላል። በዚህም ምክንያት በርካታ የግንባታ ዘርፎች እንድም ከገበያው ተሰናብተዋል ፣ ባለህበት ሂድ ሆነዋል ወይም የቁልቁሊት ጉዞ ላይ ናቸው። በዚህም ምክንያት የዘርፉ ተዋናዮች፣ ባለሙዎች እና ባለድርሻ አካላት መጪው ጊዜ ዘርፉ የሚያንሰራራበት እንዲሆን በጉጉት ይመለከታሉ።

እንደ ዕድል ሆኖ አለማቀፉ የግንባታ ዘርፍ መጻዒ ጉዞው ብርሃናማ እንደሚሆን ዜናዎች ምስራች አሰምተዋል። ምስራቹ የተበሰረው በኦክስፎርድ ኢኮኖሚክስ የዘርፉ የምጣኔ ሃብት ባለሙያዎች ቡድን የአለም ግንባታና ምህንድስና ኢንዱስትሪን አስመልክቶ ባካሄደው አጠቃላይ ጥናት ነው። እንደ ጥናቱ ዋቢነት ከሆነ መጪዎቹ አመታት ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ብርሃናማ ናቸው ።

በመጪዎቹ 15 ዓመታት ዘርፉ በ2022 ከነበረበት 9 ነጥብ 7 ትሪሊዮን የአሜሪካን ዶላር የገበያ ድርሻ በ4 ነጥብ 2 ትሪሊዮን የአሜሪካን ዶላር ከፍ በማለት እንደ አውሮፓውያኑ የዘመን ቀመር በ2037 ላይ ወደ 13 ነጥብ 9 ትሪሊዮን የአሜሪካን ዶላር ይመነደጋል። ቻይና፣ ዩናይትድ ስቴት እና ህንድ ከዚህ አማላይ የገበያ ዕድል ውስጥ የአንበሳውን ያህል ድርሻ ወደ ካዝናቸው ለማስገባት አልመዋል። በተጨማሪም በዘርፉ የደረጃ ሰንጠረዥ ላይ የሚገኙት 10 ሀገራት በ2037 የዘርፉን 70 በመቶ የገበያ ድርሻ በእጃቸው ለማስገባት አልመዋል።

እንደ ጥናቱ ከሆነ ከእነዚሁ ሀገራት ውስጥ የእስያ ታይገር ኢኮኖሚ የተሰኙት ሆንግኮንግ፣ ሲንጋፖር፣ ደቡብ ኮሪያ፣ እና ባንግላዲሽ የዚሁ ምድብተኞች ለመሆን ቀርጠው ተነስተዋል። ይህ የአለማቀፉ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ መጪው ወርቃማ ዕድል ለሀገራችን የኢንዱስትሪው ዘርፍ ምስራች ቢሆንም የገበያው ተቋዳሽ ለመሆን ብርቱ ፉክክርን ይጠይቃል። ያው ቢታሰብ በገሌ ነው የሚል ፈሊጥ አይታሰብም።

ሀገራዊ የግንባታው ዘርፍ ከፍ ሲል በተመለከተው የዘርፉ ዓለማቀፍ የቀጣይ አስርት ዓመታት የገበያ ውቅያኖስ ውስጥ መሆኑን ልብ ይሏል። ምርጫውም በገበያው ውቅያኖስ ውስጥ ብርቱ ዋናተኛ መሆን ወይም ሰጥሞ መቅረት ነው። እናም በዚህ ግዙፍ አለማቀፍ የኢኮኖሚ ጽኑ ፉክክር ውስጥ ሀገራዊ የግንባታውን ዘርፍ ህልውና ለማስጠበቅ ወደ ውስጥ መመልከት፣ የቤት ስራዎችን አጠናቆ ተሰላፊ መሆን ይገባል።

ይህንን ከባቢያዊ ሁኔታ የተነበየና ኢላማ ያደረገ የጋራ ግንዛቤና ተግባቦትን መፍጠር፣ ስትራተጅ ነደፎ መታተር እና ስርነቀል ለውጥ ማድረግ ያስፈልጋል።

በዋናነትም በጊዜ የለንም አስተሳሰብ የተቃኘ የዘርፉ ከባቢያዊ ሁኔታን እውን ለማድረግ የሚያስችል የተጠና፣ ተከታታይ የሆነ ስርነቀል የአስተሳሰብ ግንባታ ማካሄድ ያስፈልጋል። እንዲሁም የሀገር ፍቅርን፣ የሙያ ስነምግባርን፣ ምጡቅ የምህንድስና ጥበብን ተላብሰው ኃላፊነታቸውን መወጣት የሚችሉ፤ ተልዕኳቸውን በብቃት፣ በጥራት እና በውጤታማነት መወጣት የሚያስችል ክህሎትን፣ዕውቀትንና አመለካከትን የተላበሱ የኢንዱስትሪው ተዋናዮችን የማፍራት ጉዳይ ይዋል ይደር የሚያስብል አይደለም።

በተጨማሪም በፕሮጀክት ግንባታ ውስጥ የሚሳተፉ አካላት ማለትም ገንቢዎች አስገንቢዎች፣ መሐንዲሶች፣ ንዑስ ተቋራጮች፣ ግብዓት አምራቾችና አቅራቢዎች ብሎም የዘርፉ ተዋናዮችና ባለድርሻ አካሎች የተናበበና የተባበረ ብሎም ከዘመን ጋር የሚራመዱ የአሰራር ስርዓቶችን መቃኘትና ማስፈን አለባቸው።

የትምህርትና የሚዲያ ተቋማት፣ የዘርፉ ሙያ ማህበራት፣ የምህንድስና ባለሙያዎች፣ ወዘተ እጅና ጓንት ሆነው ለዘርፉ ስርነቀል ለውጥ በጊዜ የለንም አስተሳሰብ መረባረብ አለባቸው። ከፕሮጀክት ቀረጻ አንስቶ እስከ ግንባታ ክዋኔዎችና ፍጻሜ ድረስ ፕሮጀክቶችን በጥራት፣ በታለመላቸው ጊዜና ዋጋ የማጠናቀቅ ባህል መዳበር አለበት። ሀገራዊ ኢንዱስትሪው ከሰብዓዊና አካባቢያዊ ስጋት የተላቀቀ መሆን ይጠበቅበታል። እንዲሁም ዘርፉን ከብልሹ አሰራር ማጽዳት ለነገ የሚባል አይደለም። የግንባታ ህጎች፣ ኮዶችና ስታንዳርዶችን ማስጠበቅ ለአንድ ወገን ብቻ የሚተው ሳይሆን የዘርፉ ተዋናዮችና ባለድርሻ አካላት ቀርጠኛ ርብርብን ይሻል።

በአጠቃላይ መጪው አለማቀፍ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ገፀ-በረከትን ይዞ እንደሚመጣ ተበስሯል። ወደዚህ ጸጋ የሚደረገው ጉዞው የሚጀመረው ግን ዛሬ ነው። በዚህ የብስራት ደወል ውስጥ በንቃትና በትጋት የሚደረገው የጉዞ መጀመሪያው ዛሬ ነው። ዛሬ ሳብ ይፈልጋል። ዛሬ ጀምር የመፈፀም ጥበብ ይፈልጋል። ይህ ሲሆን ሀገራዊ የግንባታው ዘርፍ በአለማቀፍ የዘርፉ ምጣኔ ሃብት ፉክክሩ ውስጥ ቋሚ ተሰላፊነቱ እርግጥ ይሆናል።

ያኔ ኢትዮጵያን አፍሪካዊት የብልፅግና ተምሳሌት በማድረግ ረገድ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የአንበሳውን ድርሻ ያህል ሚና ይጫወታል።

ምንጭ፡- Global Construction Review



## ኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለስልጣን ስልጣንና ተግባራት

.1.አስማቀፋዊና ሀገር አቀፋዊ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ፣ ኮድ፣ ስታንዳርድና ደረጃ ያዘጋጃል ያሻሽላል፡፡

2.በሀገር ደረጃ የወጡ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ አዋጆች፣ ደንቦች ፣ ኮዶች፣ ስታንዳርዶች ፣ ደረጃዎች፣ መመሪያዎች መተግበራቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ የእርምት እርምጃ ይወስዳል፣ የአቅም ግንባታ ስራዎች ያከናውናል ፡፡

3.በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪና ብቃት ያለው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ እንዲፈጠር በዲዛይን፣ በጨረታ፣ በኮንትራት ይዘትና አስተዳደር እንዲሁም በግንባታ ጥራትና ቁጥጥር ግልፅና ተጠያቂነት ያለው የሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣ ይቆጣጠራል፡፡

4.በሀገሪቷ ውስጥ የሚገነቡ ማንኛውም የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች እና የመንግስት ፕሮጀክቶችን ይመዘግባል፣ ይቆጣጠራል

5..ስመሰረተ ልማት እና ኮንስትራክሽን ስራዎች ግንባታዎች ሞዴል ስፔስፊኬሽን ፣ የልኬት ስርዓትና ማኑዋል ያዘጋጃል፣ ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣ ይቆጣጠራል

6.የመንግስት ኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች በተገባላቸው በጨረታና ውል መሰረት በዲዛይን፣ በዋጋ፣ በጥራትና ጊዜ ተሰርተው ስለመጠናቀቃቸው እና ርክክብ ስለመደረጉ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ የእርምት እርምጃ ይወስዳል

7.በፌዴራል፣ በክልል እና በከተማ አስተዳደር ያለው የግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ፣ የቁጥጥርና የምዝገባ ስራ ተመጋጋቢና ተደጋጋፊ እንዲሆን የሚስችል ግልፅነትና ተጠያቂነት የሚረጋግጥ አሰራር ይዘረጋል አፈፃፀሙን ይከታተላል

8.የኮንስትራክሽን ስራዎች በአካባቢ፣ በሰራተኞች እና በህብረተሰቡ ጤንነትና ደህንነት ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ ስመከላከል የሚስችሉ አሰራርችን በእራሱ ወይም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይዘረጋል፣ አፈፃፀማቸውን ይቆጣጠራል

9.በኮንስትራክሽን ስራዎችና ግንባታዎች የአደጋ አጋጣሚዎች ሲፈጠሩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይፈትሻል፣ ሪፖርት ያቀርባል፣ የህግ ተጠያቂነት እንዲኖር ይከታተላል

10.የግንባታ ሞዴል ዋጋዎች እና የግምት መስሪያ ቀመሮች ያዘጋጃል፣ በዚሁ መሰረት የዋጋ ግምቶች በአግባቡ ስለመዘጋጀታቸው ይቆጣጠራል፣ ያረጋግጣል

11.. በኮንስትራክሽን ዘርፍ የሚሰማሩ ማንኛውም ባለሙያዎችን ይመዘግባል፣ የሙያ ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፣ ያግዳል፣ ያሳግዳል፣ ይሰርዛል፣ ወይም ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል

12.ከአንድ በላይ በሆኑ ክልሎች ውስጥ መስራት ለሚችሉ ስራ ተቋራጮች፣ አማካሪዎች እና በዘርፉ የሚሳተፉ ሌሎች ድርጅቶችን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፣ ያግዳል ይሰርዛል፣ ወይም ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡

13.ስኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የሚገለገል መረጃ ይሰበስባል፣ የመረጃ ቋት ያቋቁማል፣ ያገለብታል፣ ደህንነቱን ይጠብቃል፣ ወቅታዊና ተደራሽ ያደርጋል

14.የኮንስትራክሽን ግብዓቶችን ደረጃ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ያዘጋጃል፣ የሻሽላል፣ አፈፃፀሙን ይቆጣጠራል

15.ከውጭ የሚገቡ የግንባታ ግብዓቶች በሀገር ውስጥ ግንባታ መተካት የሚያስችል አሰራር ስርዓት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይዘረጋል፣ አፈፃፀሙን ይቆጣጠራል

16.በመንግስት የኮንስትራክሽን ስራዎች ለሚፈጠሩ አስመግባባቶች በመደበኛ ፍርድ ቤት የሚሰጡ አገልግሎቶች እንደተጠበቀ ሆኖ ባለስልጣኑ በሚዘረጋው አሰራር ስርዓት በአማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች መፍትሄ እንዲያገኙ ያደርጋል

17.የመንግስት ኮንስትራክሽን ፕሮጀክት አፈፃፀም ከጊዜ ከወጪ እና ከጥራት አንጻር ክንውኑን ኦዲት ያደርጋል፣ በሚገኙ ክፍተቶች ላይ የመፍትሄ እርምጃ ይወስዳል

18.ስውጭ አገር ዜጎች በሀገራችን የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ እንዲሳተፉ ስባለሙያዎች የሙያ ፈቃድ ይሰጣል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር አፈፃፀሙን ይቆጣጠራል

19.በተሰጠው የስልጣን ወሰን የጥናትና ምርምር ስራዎችን ይሰራል

20.ዘመናዊ የኮንስትራክሽን ስራዎች ግብአትና ውጤቶችን ጥራት መፈተሸ ላቦራቶሪ በተመረጡ ቀጠናዎች በማቋቋም አገልግሎት ተደራሽ እንዲሆን ያደርጋል

21.ስሚሰጠው አገልግሎት በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ መሰረት ክፍያ ያስከፍላል

22.የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል ፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል

## የኮንስትራክሽን ኦዲትና ኢንስፔክሽን የሚከናወኑ ቁልፍ ተግባራት



የመንግስት ኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶችን ኦዲትያደርጋል፣በሚገኙ ክፍተቶች የማስተካከያ እርምት እርምጃ ይወስዳል፤

በዓለም አቀፍ ደረጃ የወጡ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ አዋጆች፣ ደንቦች፣ ኮዶች፣ስታንዳርዶች፣ደረጃዎች መመሪያዎች መተግበራቸውን ይከታተላል፣ የእርምት እርምጃ ይወስዳል፤

በክልልና ከተማ አስተዳደር ያለው የግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ፣የቁጥጥር እና የምዝገባ ስራ ተመጋጋቢና ተደጋጋፊ እንዲሆን የሚያስችል ግልጽነትና ተጠያቂነት የሚያረጋግጥ አሰራር እንዲዘረጋ በማድረግ፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤ የኢንስፔክሽን ስራ ይሰራል፡፡

የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች አጠቃላይ አፈጻጸማቸው ከብክነት፣ ከሙስና እና ከብልሹ አሰራር የጸዱ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች በአግባቡ እንዲቀረጹ፣ ለተፈለገው አላማ እንዲገነቡና ለዲዛይን አድሚያቸው ያህል እንዲገለግሉ፣ ለሚጠበቅባቸው የጥራት ደረጃ ፣ በታቀደላቸው ጊዜና በጀት እየተሰሩ ስለመሆናቸው ፍተሻ በማድረግና ግብዓት በመስጠት፣ ብክነት እንዲቀንስ የሚደረግበት እንዲሁም የተሻሉ አፈጻጸሞች እንዲስፋፉ ለማድረግ ስነድ የሚሰነድበት ሂደት ነው፡፡



## ግንባታ እና የአካልጉዳተኞች አካታችነት

የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለስልጣን የፌዴራል መንግስት አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ 1263/2014 እንዲሁም በሚኒስትሮች ምክር ቤትደንብ ቁጥር 524/2015 የተቋቋመ ነው፡፡

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን ወደላቀ ደረጃ ለማድረስ የግንባታ ፕሮጀክቶች በተገቢው ወጪ፣ጊዜና ጥራት መፈጸማቸውን እንዲሁም የዜጎችንና የአካባቢ ደህንነትንና ጤንነትን መጠበቃቸውን በማረጋገጥ ዜጎችን ተጠቃሚ ማድረግ ከተቀቋማችን ዓላማዎች መካከል አንዱና ግንባር ቀደሙ ነው፡፡

በኢትዮጵያ የግንባታ ፕሮጀክቶች እንዲሁም የከተሞች ገፅታ ለአካል ጉዳተኞች የሚመጥን መሠረተ ልማት አውታር ግንባታ አለመኖር እና አገልግሎት አሰጣጥ ጉድለት ምክንያት በርካቶችን ለከፍተኛ እንግልት እና የጤና ችግር እየዳረጋቸው ነው።

በዋናነትም በከተሞች ውስጥ በህንጻ ግንባታዎች፣ በመዝናኛ ስፍራዎች፣ በመንገድ ግንባታዎች፣ በማህበራዊ አገልግሎቶች ግንባታዎች በግብይት ቦታዎች በመኖሪያ ግንባታዎች፣ በስብሰባ አዳራሾች በሆቴሎች፣ በህክምና ተቋማት ወዘተ ይኸው እውነታ ይስተዋላል፡፡

በተጨማሪም በአለም አቀፍ ህጎች መሰረት አካል ጉዳተኞች በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ውስጥ ከሌሎች እኩል የስራ ቅጥር ተወዳዳሪ መሆን እንዳለባቸው፤ እንዲሁም አካል ጉዳተኞችን ቀጣሪዎች ለአካል ጉዳተኞች የሚመጥን የስራ ዕድል ከመስጠት ባሻገር የስራ ቦታ ላይ ደህንነታቸውን የማስጠበቅም ህጋዊም ሆነ ሰብዓዊ ሀላፊነታቸው እንደሆነ ቢደነገግም በሀገራችን በኢንዱስትሪው ውስጥ ይህንን ከመተግበር አንጻር ውሱንነቶች እንዳሉ ግልጽ ነው፡፡

ግንባታዎች ለአካል ጉዳተኞች ምቹ ሆነው መገንባታቸው በሀገራዊ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ አውዶች ውስጥ በንቃት የሚሳተፉ፣ ለሀገራዊ የብልጽግና ጉዞ ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱ በማድረግ ረገድ ሚናው የጎላ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለስልጣንም ከተሰጡት ስልጣንና ተግባራት ውስጥ ዋነኛው በህገ መንግስቱ የተደነገገውን እና የዜጎችን ደህንነትና

ከገጽ 4
## የቀጠለ....የአካል ጉዳተኝነት

ጤንነት በማስጠበቅ ረገድ በሚያካሂዳቸው የቁጥጥር ስራዎች ላይ ዋነኛ የትኩረት አቅጣጫ ነው፡፡

በዋናነት ፕሮጀክቶች ላይ ከዲዛይናቸው ጀምሮ እስከ ፍጻሜያቸው ድረስ በሚደረግ የቁጥጥር ስራ የአካል ጉዳተኞችን አካታችነት፣ ተደራሽነት እና ምቹነት በሚያረጋግጥ መልኩ እንዲሆን ማስቻል እንዲሁም የተዛቡ አመለካከቶች ላይ ሰፊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ተግባራትን ማከናወን ዋነኞቹ ናቸው፡፡

ይህ እውን እንዲሆንም የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለስልጣን ከኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞች ማህበራት ፌዴሬሽን እና መሰረታዊ የመንገድ አገልግሎት ለአካል ጉዳተኞች ማህበር ጋር በጋራ ለመስራት በቅርቡ የመግባቢያ ስምምነት አካሂዷል፡፡

የአካል ጉዳተኞችን ተደራሽነት እውን ለማድረግ በግንባታዎች ላይ ምቹ ሁኔታን የመፍጠር ሃላፊነት የገንቢዎች፣ የአስገንቢዎች ቀልፍ ተግባራቸው መሆኑን ተገንዝበው ተግባራዊ እንዲያደርጉ ማስቻል የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለስልጣን የቁጥጥር ስራው ዋነኛ ተግባር አድርጎ ይተጋል፡፡ እንዲሁም የህግ ማዕቀፎችን በማልማት እና በማስገንዘብ ብሎም ተግባራዊ እንዲሆኑ ክትትል እና ቁጥጥር በማድረግ ረገድ ተቋማችን በቀጣይ በስፋት የሚሰራ ይሆናል፡፡

በአጠቃላይም የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ራዕይን እውን ለማድረግ በሚካሄደው ሀገራዊ ርብርብ ውስጥ የአካል ጉዳተኞች ደህንነታቸው፣ ክብራቸው መብታቸው እንዲጠበቅ እና እንዲከበር ለማድረግ በዘርፋችን ያሉ ተዋናዮች እና ባለድርሻ አካላት አወንታዊ ሚና መጫወት ይጠበቅባቸዋል፡፡

### አካል ጉዳት እና የአካል ጉዳተኝነት ጉዳይ የመላው የሰው ልጆች ጉዳይ ነው!

## የኮንስትራክሽን ግጭቶች አፈታት ሥራ አስፈፃሚ ዋና ዋና ተግባራት

### የተሰጠ ስልጣንና ተግባር

የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለስልጣን በደንብ ቁጥር 524/2015 ከተሰጡት ስልጣን እና ተግባራት መካከል በአንቀፅ 5(16) ስር ባለስልጣኑ በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ውስጥ የሚነሱ አለመግባባቶችን በአማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች መፍትሔ እንዲያገኙ ያደርጋል በሚል ተደንግጓል፡፡

የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለስልጣን የኮንስትራክሽን ግጭቶች አፈታት መሪ ስራ አስፈጻሚ ግጭቶች ወደ ፍርድ ቤት ከመሄዳቸው በፊት አማራጭ የግጭት አፈታት (አ.ግ.አ) ዘዴዎችን በመጠቀም ለግጭቶች መፍትሔ ያስገኛል፣ በዚህም ሂደት የሚከተሉትን ውጤቶችን ያረጋግጣል፣

⊠ ተዋዋዮች አለመግባባቶቻቸውን በራሳቸው የተመረጡ የአ.ግ.አ ዘዴዎችን ተጠቅመው መፍታታቸውን፣

⊠ በተከራካሪ ወገኖች መካከል መልካም ግንኙነት በማስቀጠል፣

⊠ ከህግ ሙያ ውጪ ያሉ የኮንስትራክሽን ባለሙያዎችን በአ.ግ.አ ዘዴዎች ላይ መሳተፋቸውን፣

⊠ ወደ ፍ/ቤት ክርክር ቢገባ ሊዘገይ የነበረውን የፕሮጀክት ማጠናቀቂያ ጊዜ መቀነስን ፣

⊠ ወደ ፍ/ቤት ክርክር ቢገባ ሊወጣ የሚችለውን የተከራካሪዎች ወጪ እና ፕሮጀክቱ ላይ በተለያዩ ምክንያቶች ሊፈጠር የነበረውን ተጨማሪ ወጪን መቀነስን እና

⊠ ወደ ፍርድ ቤቶች ሳይሄዱ ግጭቶች በዚሁ አማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴ ከመስማማት መደረሱን እና ፍርድ ቤት ላይ የሚፈጥረውን የሥራ ጫና መቀነስን በማረጋገጥ የግንባታ ፕሮጀክቶች ለታለመላቸው ዓላማ በተያዘላቸው ጊዜ ውስጥ እንዲውሉ የማስቻል ሥራ ያከናውናል፡፡

### ከአ.ግ.አ ዘዴዎች ውስጥ በኢ.ኮ.ባ የተመረጡ የማስፈፀሚያ ስልቶች ማከናወን

⊠ በአስማሚነት (Mediation) በመሥራት ማለት በተዋዋይ ወገኖች መካከል ያለውን አለመግባባት በስምምነት ለመፍታት ባለጉዳዮችን በማግባባት፣ ጭብጦችን በመለየት፣ በማብራራት፣ የተከሰተን ወይም ወደፊት ከውል ወይም ከውል ውጪ ባለ ሕጋዊ ግንኙነት ሊፈጠሩ የሚችሉ አለመግባባቶችን መፍታት ውጤቱንም የማስማማት የውል ስምምነት በማፈራረም መቋጨት ነው፣

ከገጽ 1

## የቀጠለ

- ከህንጻ ቁጥጥር የተገኙ ግኝቶች ከጊዜ አንጻር የመስክ ቁጥጥር ከተደረገባቸው ሰማንያ ፕሮጀክቶች ውስጥ ከአንድ ዓመት እስከ ሰባት ዓመት ግንባታቸው የዘገዩ ፕሮጀክቶች ተገኝተዋል፡፡ የጊዜ ማራዘሚያ ከተሰጣቸው ስድሳ ስድስት ፕሮጀክቶች በተሰጣቸው ጊዜ እየተከናወኑ ያሉት 59 ፕሮጀክቶች ናቸው፡፡ የፕሮጀክቶቹ አጠቃላይ የውል ዋጋ 14.99 ቢሊየን ሲሆን ከጊዜ አንጻር የተጓተቱበት ምክንያት ውስጥ የስራ ተቋራጩ በፕሮግራም ያለመመራት፣ የተሟላ የግንባታ ግብዓት በሳይት ላይ ያለማቅረብ በተቋራጩ በኩል፣ የሳቦራትሪ ፍተሻ ውጤት በወቅቱ ያለማቅረብ፣ ዋጋ ካልተስተካከለ ሳለመሥራት መወሰን፣ በአሰሪው መ/ቤት በኩል የወሰን ማስከበር ችግር፣ አሳግባብ የውል ማሻሻል ሂደቶች፣ ለዋጋ ማሻሻያ ጥያቄዎች ወቅታዊ ምላሽ ያለመስጠት፣ የተሰሩ ሥራዎች ክፍያ ማዘግየት፣ የአቅም ውስንነት ተጠቃሽ ምክንያቶች ናቸው፡፡

- በህንጻ ቁጥጥር የተገኙ ግንቶች ከጥራት አንጻር ሲታዩ ቁጥጥር ከተደረገባቸው ውስጥ ሰሳሳ አንድ የህንጻ ፕሮጀክቶች ላይ የጥራት ችግር እንዳለባቸው ተገምግሟል፡፡ የጥራት ጉድለታቸው የዲዛይን፣ ሳቦራቶሪ ምርመራ ውጤቶችን በሳይት ላይ ያለማስቀመጥ፣ ወቅቱን የጠበቀ የኢንስፔክሽን ሰርትፊኬት ያለማዘጋጀት፣ በሳይት ላይ ሲተገበሩ የሚችሉ የጥራት ማረጋገጫዎች ያለመመቻቸት፣ በዲዛይንና ሥራው ዝርዝር መሰረት ያለመገንባት፣ ርክክብ የተደረጉ ህንፃዎች ተዘግተው መቆየት ተጠቃሽ ምክንያቶች ናቸው፡፡
- ከደህንነት አንጻር የህንጻ ፕሮጀክቶች ሀያ አራት ሳይቶች ላይ ምንም አይነት የስራ ላይ ደህንነት መጠበቂያዎችም ሆነ ምልክቶች በመስሪያ ቦታው አልተተገበሩም እንዲሁም ሰራተኞች ለድንገተኛ አደጋ ተጋላጭ በሆነ መልኩ ስራዎችን ሲሰሩ መታየቱን መገምገም ተችሏል፡፡ በተጨማሪ በአንድ/1 ፕሮጀክት ላይ የሞት አደጋ ደረሷል፡፡
- የህንጻ ፕሮጀክቶቹ ለአካል ጉዳተኛ ተደራሽ ያልሆኑ (የራምፕ እና የመፀዳጃ ቤት ስታንዳርድ አለመጠበቅ) በሳይት ቦታ የመፀዳጃና ልብስ መቀየሪያ ለብቻ ያልተዘጋጀ መሆኑ በቁጥጥር የተገኙ ግኝቶች ሆነው ተመዝግበዋል፡፡
- በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለስልጣን ኮንስትራክሽን ግብዓት ቁጥጥር ስራ አንዱ ሲሆን በስድስት ወር የቁጥጥር ስራ ውስጥ በግንባታ ግብዓት ጥራት ላይ ክፍተት በፈጠሩ አካላት ላይ ከሚመለከተው አካል ጋር በመተባበር የእርምት እርምጃ ለመውሰድ አቅዶ በመስራት በቢሮም ሆነ በማምረቻ ቦታ የጥራት መፈተሻ መሳሪዎች የካሳብሬሽን ሰርተፍኬት ያለመኖር፣ በፋብሪካ በካይ ጭስ ወደ ከባቢ አየር መልቀቅ፣ የአርማታ ብረት ላይ የጥንካሬ ደረጃ አለማተም እና የምርት እና የሳብራቶሪ መሳሪያዎች የታደሰ የካሳብሬሽን ሰርተፍኬት የሌላቸው በመሆኑ እና የጥራት መፈተሻ ሳብራቶሪ መሳሪያዎች የታደሰ የካሳብሬሽን ሰርተፍኬት የሌላቸው ፋብሪካዎችና አቅራቢዎች በመገኘታቸው የተገኘባቸውን ክፍተት በአጭር ጊዜ ማስተካከል እንዲችሉ የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ተጽፏል፡፡

ከገጽ 5

## የቀጠለ...አማራጭ የኮንስትራክሽን የግጭት አፈታት

⊠ **በእስታራቂነት** (Conciliation) በመሥራት ማለት በተዋዋይ ወገኖች መካከል ያለውን አለመግባባት በስምምነት ለመፍታት ባለጉዳዮችን በማግባባት፣ ጭብጦችን በመለየት፣ በመገምገም፣ በማብራራት፣ የመፍትሔ ሀሳቦችን በማቅረብ የተከሰተን ወይም ወደፊት ከውል ወይም ከውል ውጪ ባለ ሕጋዊ ግንኙነት ሲፈጠሩ የሚችሉ አለመግባባቶችን መፍታት፣ ውጤት በሁለቱ መካከል ይግባኝ ሳይኖረው እንደተሰጠ የመጨረሻ ፍርድ ተቆጥሮ በሕግ ፊት የፀና እንዲሆን በማድረግ ስምምነት በማፈራረም መቋጨት ነው፣

⊠ **በባለሙያ ብይን** (Expert Determination) መሠረት በመሥራት ማለት ግጭቶችን ለመፍታት በሚደረግ ጥረት ውሥጥ በተለየ የዕውቀት ፍላጎት መሠረት በልዩ ክህሎት እና ዕውቀት በመታገዝ የሚቀርብ የባለሙያ የውሳኔ ብይን ነው፤ ውጤት በሁለቱ መካከል እንደ ባለሙያ ብይንና ውሳኔ ሆኖ እንዲያገለግል በማድረግ መቋጨት ነው፣

# ኢኮባ በስድስት ወር 116 የመንግስት የግንባታ ፕሮጀክቶች ላይ ቁጥጥር አከናውኗል

## • 60 የግንባታ ፕሮጀክቶች ዲዛይን ላይ በተካሄደ ግምገማ 1 ነጥብ 1 ቢሊዮን ብር ማስቀነስ ተችሏል

የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለስልጣን በአዋጅና ደንብ ከተሰጡት ስልጣንና ተግባራት መካከል በመንግስት በጀት የሚከናወኑ የህንፃ፣ የውሃና ኢነርጂ እንዲሁም የትራንስፖርትና ኮሙዩኒኬሽን ግንባታ ፕሮጀክቶችን መቆጣጠር አንዱ ነው፡፡

በዚሁ መሰረትም በ2016 ዓ.ም ግማሽ አመት ውስጥ የውስታ ዋጋቸው 65 ቢሊዮን ብር የሚጠጋ 116 የመንግስት የግንባታ ፕሮጀክቶች ላይ የአፈፃፀም ክትትልና ቁጥጥር ስራ ተከናውኗል፡፡ እንዲሁም 8 ነጥብ 1 ቢሊዮን ብር ግምታዊ ዋጋ የተቀመጠላቸው 60 ያህል የመንግስት የግንባታ ፕሮጀክቶች ላይ የዲዛይን ግምገማ ተከናውኗል፡፡

ለዲዛይን ግምገማ ከቀረቡት 60 ፕሮጀክቶች በተከናወነ ቴክኒካል የምህንድስና ግምገማ ስራ የተጋነነ ዋጋ ላይ ማስተካከያ የተካሄደ ሲሆን በዚሁ መሰረት 1 ነጥብ 1 ቢሊዮን ብር ማዳን ያስቻለ ተግባር ተከናውኗል፡፡

እንዲሁም የግንባታ ኮዶችና ስታንዳርዶችን፣ ወቅታዊ የገበያ አዝማሚያዎችን እና የግዥ መመሪያን ባሟላ መልኩ ዲዛይኖቹ ስለመዘጋጀታቸው የማረጋገጥ፣ ግድፈት ያለባቸውም የማስተካከያ እርምት እንዲያከናውኑ የማድረግ ተግባር ተፈፅሟል፡፡

በተመሳሳይ 116 በሚሆኑ የህንፃ፣ የትራንስፖርትና ኮሙዩኒኬሽን፣ እንዲሁም የውሃና ኢነርጂ የግንባታ ፕሮጀክቶች ላይ በተካሄደ የአፈፃፀም ክትትል ስራ ፕሮጀክቶቹ ላይ ከጥራት፣ ከወጪ፣ ከጊዜ እንዲሁም ከጤንነትና ደህንነት አንፃር ቁጥጥር ተካሂዷል፡፡

ግንባታዎቹ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እንዲሁም ልዩ ልዩ የፌዴራል ተቋማት የሚያስገነቧቸው ናቸው፡፡

በርካታ ፕሮጀክቶች አፈፃፀማቸው ከውስታ ጊዜያቸው በአማካይ ከአንድ እስከ ሰባት አመት የዘገዩ ናቸው፡፡ እንዲሁም ከዋጋ እና ከጤንነትና ደህንነት አንፃርም በርካታ ክፍተቶች ተገኝተዋል፡፡ በዋናነትም ለ15 ፕሮጀክቶች የተከናወነ ቅድመ ክፍያ 1 ነጥብ 3 ቢሊዮን የሚጠጋ ብር ሲሆን ተመላሽ የተደረገው ወደ 200 ሚሊዮን ብር የሚጠጋ ነው፡፡ ከ823 ሚሊዮን ብር በላይ ተመላሽ አለመደረጉ በቁጥጥር ስራው ተረጋግጧል፡፡

ለአፈፃፀም ክፍተቶቹ መንስኤዎቹ የዲዛይን ለውጥ ፣ የጉዳት ካሳ ክፍያ በወቅቱ አለመፈፀም፣ የወሰን ማስከበር ችግር፣ የስራ ተቋራጮች በፀደቀ የስራ መርሃ ግብር አለመመራት፤ የግንባታ ግብዓት እጥረት እንዲሁም የሚፈጠር የዋጋ ጭማሪ፤ ለግንባታ ስራ የሚያስፈልጉ ማሽነሪዎች እና መሳሪያዎች በሳይት ላይ ተሟልቶ አለመቅረብ ፤ በግንባታ ወቅት የሚያጋጥሙ ተገማች ያልሆኑ ሁኔታዎች፤ የክፍያ መዘግየት ፣ በአማካሪ የሚፈጠር የኮንትራት አስተዳደር ችግር፣ በባለቤትና በአማካሪ የሚፈጠር የውሳኔ መዘግየት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በአፈፃፀም ክትትልና ቁጥጥር ስራው የታዩና አግባብነት የሌላቸው ክፍተቶች ላይ እንደየግድፈቶቹ መጠንና ዓይነት ተገቢ እርምት እንዲደረግባቸው ለሚመለከታቸው አካላት ግብረመልስ የተሰጠ ሲሆን፣ በቀጣይ በዚሁ አግባብ ስለመፈፀማቸው የማረጋገጥ ስራ ይከናወናል፡፡

**የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለስልጣን**